FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF WATER AND ENERGY

Ethiopian Meteorological Institute Meteorological Forecast and Early Warning Research


# SEASONAL CLIMATE ASSESSMENT & FORECAST BULLETIN

## አጽህሮት

Issued: Feburary, 2023

**Climate Monitoring and Forecast Services for Different sectors:**

**Agriculture**



**Disaster Risk Management**



**Water Resource Management**



**Environment & Health**



**Transport**




**Construction**



https;//www.ethiomet.go

- የበጋ ወቅት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ በተለይም በጥቅምትና በህዳር ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የበጋ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛዉ በታች ዝናብ ያገኙ ሲሆን፣ በሃገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንዲኖር ምክንያት ሆኗል።
- በታህሳስና ጥር ወራት ግን በምሥራቅ አውሮፓ የሚገኘው የሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት (Siberian high pressure) በአረብ ምድር በኩል ወደ አገራችን በመግባቱ በተጠቀሱት ሁለት ወራት ደረቅና ቀዝቃዛ አየር በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደተከሰተ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
- በአሁኑ ጊዜ በከባቢ አየርና በውቅያኖሶች ላይ በመታየት ላይ የሚገኙትና ለቀጣዮቹ ወራት በተተነበዩት መረጃዎች ላይ መሰረት ተደርጎ እ.ኤ.አ የ2006፣ 2001 እና 2021 ዓመታት ከዘንድሮው የበልግ ወቅት ጋር ተመሳሳይነት እንደሚኖራቸው (Analogue Years) ግንዛቤ ተወስዷል።
- *በዚህም መሠረት 2023 የበልግ ወቅት ከሞላ ጎደል መደበኛ የውቅያኖስ ሙቀት (Enso-Neutral) እና IOD-Neutral ሁኔታ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤በሀገሪቱ ሰሜን አጋማሽ፣ መካከለኛው እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛው በታች ዝናብ ይኖራቸዋል።*




□□□□ 2015

## ይዘት

ይዘት ........ i
እ.ኤ.አ 2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና የ2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 1
አ ህ ፅ ሮ ት (Executive Summary) ........ 1
እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 3
1.1 መግቢያ ........ 3
1.2 እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ አጠቃላይ ግምገማ ........ 3
1.2.1 የዝናብ ሁኔታ ........ 3
1.2.2 የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ሁኔታ ........ 8
1.2.3 እ.ኤ.አ በ2022/23 በጋ ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ ከተተነበየው ጋር ሲነጻጸር ........ 9
1.3 እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት በየክልሎች የነበረው ገፅታ ........ 9
1.3.1 አፋር ........ 9
1.3.2 ትግራይ ........ 9
1.3.3 አማራ ........ 10
1.3.4 ቤንሻንጉል ጉሙዝ ........ 10
1.3.5 ጋምቤላ ........ 10
1.3.6 ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ........ 11
1.3.7 ኦሮሚያ ........ 11
1.3.8 ሶማሌ ........ 12
1.3.9 ሐረሪ ........ 12
1.3.10 ድሬዳዋ ........ 12
1.3.11 አዲስ አበባ ........ 13
1.3.12 ደቡብ ምዕራብ ........ 13
1.3.13 ሲዳማ ........ 13
ምዕራፍ ሁለት ........ 14
2.0 እ.ኤ.አ የ2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 14
2.1 መግቢያ ........ 14
2.2 የበልግ ወቅት የዝናብ አማካይ ገጽታ ........ 14
2.3 የበልግ ወቅት የዝናብ ድርሻ ........ 16
2.5 በበልግ ወቅት የሚስተዋለው የሙቀት ሁኔታ ........ 16
2.6. እ.ኤ.አ 2022/23 በልግ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ አሰጣጥ ........ 17

2.6.1. አፋር ........ 18
2.6.2. ትግራይ ........ 18
2.6.3 አማራ ........ 18
2.6.4. ቤንሻንጉል ጉሙዝ ........ 19
2.6.5 ጋምቤላ ........ 19
2.6.6 ኦሮሚያ ........ 20
2.6.7. ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ........ 20
2.6.8. ሶማሌ ........ 21
2.6.9 አዲስ አበባ ........ 21
2.6.10 ድሬዳዋ ........ 22
2.6.11. ሐረሪ ........ 22
2.6.12. ሲዳማ ........ 22
2.6.13. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ........ 23
ምዕራፍ ሶስት ........ 27
3.1 እ.ኤ.አ የበጋ 2022/23 ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 27
3.2 እ.ኤ.አ በ2022/23 የበጋ ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በዉሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረዉ ተፅዕኖ ........ 31
3.3 የበጋ 2022/23 ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 33
ምዕራፍ አራት ........ 35
4.1 እ.ኤ.አ 2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ በግብርና እንቅስቃሴ ........ 35
ላይ ሊያደርስ የሚችለው ተፅዕኖ ........ 35
4.2 እ.ኤ.አ የ2023 በበልግ ወቅት የሚጠበቀው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 37
........ **Error! Bookmark not defined.**
4.3 እ.ኤ.አ በልግ 2023 ወቅት የአየር ጠባይ በማህበረሰብ ጤና ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 38

## እ.ኤ.አ 2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና የ2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## አ ህ ፅ ሮ ት (Executive Summary)

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እ.ኤ.አ የ2022/23 በጋ የአየር ጠባይ ግምገማና 2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጥልቀትና በዝርዝር ቀርቧል።

በመደበኛ ሁኔታ በጋ ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ድረስ ያሉትን አራት ወራት የሚያጠቃልል ሲሆን፤ የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተዳከሙ እና የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ከሚያደርገው ማፈግፈግ ጋር ተያይዞ በምስራቅ፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሀያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚታይበት ሲሆን፦ ለደቡብና ለደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ደግሞ ከበልግ ቀጥሎ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። በበጋ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ከሚከሰቱት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጥንካሬ አንጻር በተለያዩ ዓመታት ደረቅ ወይም እርጥበታማ የአየር ጠባይ የሚዘወተርበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖውን ያሳድራል፡፡

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲቲዩት በዓመት ሦስት ጊዜ የወቅት ትንበያዎችን በማዘጋጀት ለልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት የትንበያ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ በዚሁ መሠረትም ለበጋ 2022/23 የወቅታዊ ትንበያ ተሰጥቶ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፤ በዚያን ጊዜ በተሰጠው ትንበያ መሠረት የበጋ ዝናብ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ከመደበኛው በታች እንደሚሆን ተጠቁሞ ነበር።

ባለፈው የበጋ ወቅት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ በተለይም በጥቅምትና በህዳር ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ መመዝገቡን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተቀሩት የታህሳስና ጥር ወራት ግን በምሥራቅ አውሮፓ የሚገኘው የሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት (Siberian high pressure) በአረብ ምድር በኩል ወደ አገራችን በመግባቱ በተጠቀሱት ሁለት ወራት ደረቅና ቀዝቃዛ አየር ሁኔታ በተለያዩ ደጋማ የአገሪቱ ሥፍራዎች ላይ እንደተከሰተ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይሁንና በዚህ ዓመት የነበረው

ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ያልነበረው ሲሆን፦ በጥቂት የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የምስራቅና የደቡብ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ ለጥቂት ቀናት ከተመዘገበው አነስተኛ መጠን ያለው ቅዝቃዜ ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ እንዳልነበረው መረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ ባለፈው የበጋ ወቅት በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ሥፍራዎች እንዲሁም በቦረና፣ በጉጂና በባሌ ኪስ ቦታዎች ከተመዘገበው ከመደበኛ በታች ዝናብ በስተቀር በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ ነበር፡፡

የበልግ ወቅት ከፌብርዋሪ እስከ ሜይ ያሉትን አራት ወራት የሚሸፍን ሲሆን፤ በዋነኛነት የበልግ አብቃይ የሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በቦታና በስርጭት የተሻለ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በዚህ ወቅት የሚታየው የዝናብ ስርጭትና መጠን በቦታና በጊዜ ወጥ ያልሆነና ከፍተኛ መዋዠቅ የሚታይበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በበልግ ወቅት የሚዘንበው ዝናብ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ ለሚዘሩ የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለመኸር ማሳ ዝግጅት እንዲሁም በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ቦታዎች ላይ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ እየታየ ካለው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (IOD-Neutral) እና በቀጣዮቹ የበልግ ወራት ከሚጠበቀው የፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት (Enso-Neutral) መሆኑ እና ሌሎች የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች አንጻራዊ ጥንካሬ ጋር ተያይዞ በመጪው የበልግ ወቅት በተለይም በደቡባዊው የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም በወቅቱ የሚጠበቀው የዝናብ መጠንና ሥርጭት በበልግ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ የሚስተዋለውን ተለዋዋጭ የአየር ጠባይ ግምት ውስጥ በማስገባት በግብርና ሥራ፣ በውሃ አቅርቦትና በአካባቢ እንክብካቤ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖውን መከታተልና መገምገም ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማ

### 1.1 መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በጋ ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ድረስ ያሉትን አራት ወራት የሚያጠቃልል ሲሆን፤ የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተዳከሙ እና የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ከሚያደርገው ማፈግፈግ ጋር ተያይዞ በምስራቅ፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሀያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚታይበት ሲሆን፤ ለደቡብና ለደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ደግሞ ከበልግ ቀጥሎ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። በበጋ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ከሚከሰቱት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጥንካሬ አንጻር በተለያዩ አመታት ደረቅ ወይም እርጥበታማ የአየር ጠባይ የሚዘወተርበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖውን ያሳድራል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እ.ኤ.አ በ2022/23 የበጋ ወቅት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ የታየው የዝናብ እና የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት መጠን በጊዜና በቦታ ሥርጭት አንፃር ተገምግሞ የቀረበ ሲሆን፣ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያሳደረው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖን በተመለከተም ጠቅለል ባለ መልኩ ግምገማ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም በበጋ መግቢያ ላይ ለወቅቱ የተሰጠው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትክክለኛነት ከመገምገም ጎን ለጎን በወቅቱ ውስጥ ከመደበኛው ሁኔታ ወጣ ባለ መልኩ በተከሰቱት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ ግምገማ ተደርጓል።

## 1.2 እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ አጠቃላይ ግምገማ

### 1.2.1 የዝናብ ሁኔታ

ባለፈዉ የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ እና የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በብዙ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ሰሜን አጋማሽ የሀገራችን አካባቢዎች በሁለተኛው አስር ቀናት ውስጥ በአብዛኛው ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ

የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ሽፋን የተነሳ በሰሜን፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በሌላ በኩል በወሩ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ላይ ወደ ሀገራች እየገባ የነበረው ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ጨምሮ ተስተውሏል፡፡ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸው የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናብ እንዲኖር መንስዔ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች ላይም ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረው ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ ምስራቅ አማራ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ትግራይ፣ የደቡብ ህዝቦች እና ምስራቅ አካባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በጎሬ 34.0፣ በነቀምት 39.8 እና 32.5፣ በአማን 66.1፣ በበደሌ 34፣ በቡሬ 64፣ በቦሬ 34፣ በቻግኒ 42.4፣ በጨፋ 42.4፣ በዳንግላ 51.5፣ በጊዮን 32.2፣ በጊዳያና 63.3፣ 36.2፣ 46.1 እና 64፣ በጉንዶመስቀል 34፣ በእምድብር 36፣ በኮንሶ 34.8፣ በላሬ 45፣ በሊሙገነት 46.7፣ 38.5 እና 38.8፣ በማሻ 36.4፣ 40.2 እና 30.6፣ በነጆ 40.5፣ 36.0 እና 38፣ በሸርቆሌ 36.2፣ በሰኮሩ 50.5፣ በቴፒ 31.3 እንዲሁም በተርጫ 54፣ በአቦቦ 30.4፣ በአይራ 33.2፣ በአርጆ 36.4፣ በአይከል 32.7፣ በቡርጂ 30.6፣ በቻግኒ 55.6፣ በዶሎመና 68.5፣ በጋምቤላ 34.0፣ በጊኒር 30.0፣ በጂንካ 37.9 ፣ በሻምቡ 31.2 እና በወላይታ ሶዶ 50.5 በአርባ ምንጭ 41.7፣ በአይከል 46.3፣ በባህር ዳር 35.8፣ በዶሎመና 30.3፣ በጊኒር 32.0፣ በሀገረማርያም 46.7 እንዲሁም በቀብሪደሀር 50.2 በሚሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተዘወትሮባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት ከ5 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በደብረ ብርሀን 1.8፣ 1.2 እና 2.2፣ በወገልጤና 1.8 እና 3.0፣ በቡኢ 3.8፣ በጨፋ 4.0፣ በእነዋሪ 4.6 እና 4.5፣ በፍቼ 4.2 እንዲሁም በመሀል ሜዳ 1.8 እና 3.0 በዲሴ ይገኙበታል፡፡

## እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የኦክቶበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የምዕራብና መካከለኛው ጎንደር፣ የአዊና የምዕራብ ጎጃም፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ጉምዝ ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ፤ ከኦሮሚያ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጅማ፣ የጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ እንዲሁም የባሌ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም አብዛኛው የሶማሌ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የምስራቅ አማራ ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞኖች፣ የምዕራብ አርሲና አርሲ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል።

ባለፈዉ የኖቬምበር ወር የመጀመሪያዉ እና ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስፋፍተዉ ነበረ የተስተዋሉት፡፡ በዚሁ መሰረት ዝናቡ በስርጭት ረገድ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ ያልሆኑ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ አብዛኛቹን ቦታዎችን ያዳረሰ ነበረ፡፡ ይሁን እንጂ በኖቬምበር ወር ሶስተኛዉ አስር ቀናት በመጀመሪያዉ እና በሁለተኛዉ አስር ቀናት ላይ የነበረዉ ዕርጥበት ከአብዛኛዎቹ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገራች አካባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከም በጥቂት የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ተወስኖ የቆየ ሲሆን፤ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡

በተጨማሪም ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በቁሉምሳ 95.7 እና 32.6፣ በጎዴ 30.1 እና በቡሬ 45.0፣ በሊሙገነት 42.0፣ እና በማሻ 56.4 በሚሜ ይገኙበታል፡፡በሌላ በኩል የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በተለይም ከሁለተኛዉ አስር ቀን ጀምሮ በአንፃራዊ ሁኔታ በመጠናከሩ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት መጠን በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት በደብረብርሀን 0.2፣ 2.8፣ 2.0፣

2.2፣ 3.2 4.0፣4.2፣ 0.4፣ 3.0፣ 3.4፣ 2.2፣ 4.8፣ እና 2.0፣ በሐሮማያ 1.6፣ 2.2፣ 3.4፣ 4.2፣ 1.0 ፣4.0፣ 3.0፣ 2.0፣3.0 ፣3.8፣ 3.4 እና 3.0፣ በቡኢ 3.4፣ 3.8 4.6፣4.6፣ 4.4፣ 3.0 ፣ 4.6፣ 4.6፣ እና 4.6፣ በጨፋ 4.2 4.6፣ 4.6፣ 3.4፣ 4.2፣ 4.6፣ 4.4፣ እና 4.2፣ በፍቼ 4.6፣ በመሐል ሜዳ 1.2፣ 2.0፣ 3.0፣ 3.2 እና 4.0፣ በወገል ጤና 2.0፣ 2.8፣ 3.5፣ 3.6 4.0፣ 4.0፣ 4.5፣ እና4.0፣ በእነዋሪ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.0፣ አምባማሪያም 4.6፣ 4.0፣ 3.6፣ 4.8፣ 4.6፣ እና 4.0፣ አርሲሮቤ 4.5 4.0 3.5፣ 4.5 ፣4.5 እና 3.0፣ በደባርቅ 4.8፣ በሮቤ 4.4 እና 4.2 በዳንግላ 4.0፣ እንዲሁም እንድብር 1.8፣ በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ባለፈው የኖቬምበር ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የምዕራብና መካከለኛው ጎንደር፣ የአዊና የምዕራብ ጎጃም፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ከኦሮሚያ የቄለም ወለጋ ዞኖች፣ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጅማ እንዲሁም የባሌ ዞኖች፣ የምዕራባና ምስራቅ ሀረርጌ፤ድሬዳዋ፤ከአፋር ዞን ሶስት፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በጥቂት የሶማሌ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል።

ባለፈዉ የዲሴምበር ወር ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዉና ሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉም ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብና ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል አደሌ -4.0 እና -4.0፣ በደብረብርሀን -0.8፣ 1.4፣ 4.2፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.8 እና 3.0 ፤ በሐሮማያ 0.6፣ 0.2፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.4፣ 1.0፣ 1.8፣ 1.8 እና 2.4፤ በቡኢ 4.0፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.6 እና 4.0 ፤በጨፋ 2.4፣ 2.8፣ 3.0፣ 2.4፣ 3.2፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.6፣ 4.8 እና 4.2፤ በአደሌ 4.0፣ 2.5፣ 2.2፣ 4 እና 4.5 ፤በመሐል ሜዳ 2.2፣ 2.8፣ 3.2፣ 4.5፣ 4.2፣ 4.8 እና 2.2 ፤አርሲ ሮቤ 4፣ 4.5፣ 4.5፣ 4፣ 4 እና 3.0፤ ዳንግላ 4.6፤ ደባርቅ 4.5፣ 4.5 እና 4.4፤ ደብረ ወርቅ 4.8 እና 4.8፤ጅማ 4.5 ፤ሮቤ 3.4፣ 3.6፣ 4.2 እና 4.4 ፤ነቅምት 1.0 ፤የትኖራ 4.1 እንዲሁም በወገል ጤና 4.5፣ 4.0፣ 4.0፣ 2፣ -0.2፣ 1.4፣ 2.6፣ 3.2፣ 2.6 እና 3.2 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በዲሴምበር

የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አንፃራዊ የሆነ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ጋብ ብሎ ተስተዉሏል፡፡ በሌላ በኩል ከነበረዉ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል ጋምቤላ 40.9፣ ጎሬ 35፣ ጂንካ 33.5፣ ማሻ 36.8 እና 30.4፣ ማጂ 34.2፣ ሳሁላ 51.2፣ ጂማ 37.1፣ መትሃራ 31፣ አቦምሳ 30.2፣ አይራ 30.6 እና 30.4፣ ካቺሴ 46.8 እንዲሁም በማጀቴ 66.3 እና 34.1 በሚ.ሜ ተመዝግቦባቸዋል።

ባለፈዉ የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የሰሜን፣ መካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ ባቲ፣ የዋግህምራ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በሰሜን ሸዋ፣ በአርሲና ባሌ ጥቂት ቦታዎች ላይ፤ ከአፋር ክልል በዱብቲና በሰመራ ዞኖች፤ በጋምቤላ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም አብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የወቅቱን ዝናብ ማግኘት የሚገባቸው የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡

ባለፈው የጃንዋሪ ወር የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አስር ቀናት ላይ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተጠናከረ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቅዝቃዜው መጠን ከ0 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል በደብረብርሀን -1.2፣ -0.8፣ በሐሮማያ -1.4፣ -1.2፣ -0.6 -0.2፣ እንዲሁም በመሐል ሜዳ -1.5 በዲግሪ ሴልሽስ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውላል፡፡ በሌላ በኩል ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር በማሣየታቸው ከነበራቸው የደመና ሽፋን በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተስተውሎባቸዋል፡፡ በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ ተስተውሏል። ሆኖም በመጀመሪያዎቹ ሁለት አስር ቀናት በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን

ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን መጨመር ተስተውሏል።

በጃንዋሪ ወር በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በዋግህምራ፣ በሰሜንና በመካከለኛው ጎንደር እንዲሁም በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ ሀረርጌና የአርሲ ዞኖች፣ በአሶሳ እንዲሁም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሸካ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው ።

በአጠቃላይ ባለፈው በጋ 2022/23 ወቅት በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ ከ200-500 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ31-60 ቀናት ያህል አግኝተዋል ። በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅና በመካከለኛው እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ በመጠኑ ከ 50-200 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ10-30 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1ሀ እና 1ለ) ፡፡

ባለፈው የበጋ ወራት በተለይም በኦክቶበርና በኖቬምበር እንዲሁም አልፎ አልፎ በዲሴምበር በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ የተስተዋለ ሲሆን በአንጻሩም በዲሴምበ እና በጀንዋሪ ወር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ነበረው፡፡ በዘንድሮው በጋ ከነበረው እርጥበታማ አየር ጋር ተያይዞ ለጥቂት ቀናት በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣በመካከለኛውና በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ ከተስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው ቅዝቃዜ በስተቀር እምብዛም የውርጭ ክስተት እንዳልነበር ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዘንድሮው በጋ ወቅት የታየው የአየር ጠባይ ክስተት ለወቅቱ ከተሰጠው ትንበያ ጋር በአብኛው ተመሳሳይነት ነበረው(ካርታ 1ሐ)፡፡

### 1.2.2 የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ሁኔታ

የበጋ ወቅት መገለጫ ከሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንክሮ መታየት እንዲሁም በአንዳንድ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ውርጭ መከሰት ነው። በዘንድሮው እ.ኤ.አ. የ2022/23 የበጋ ወቅት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት (ጥቅምት እና ህዳር) በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከደመና ሽፋን መጨመርና የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ምክንያት የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጎልቶ ያልታየ ሲሆን፣ በአንጻሩ በተቀሩት ወራት (ዲሴምበርና ጀንዋሪ) ግን አነሰተኛ መጠን ያለው ቅዝቃዜ የተስተዋለ ሲሆን፣ በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ ከዜሮ ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ቅዝቃዜ እንደነበር መገንዘብ ተችሏል ።

### 1.2.3 እ.ኤ.አ በ2022/23 በጋ ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ ከተተነበየው ጋር ሲነጻጸር

እ.ኤ.አ ለ2022/23 በጋ ወቅት በተሰጠው ትንበያ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በደቡባዊና በምሥራቃዊ አጋማሽ ላይ የበጋው ወቅት ዝናብ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በታች ሊሆን እንደሚችል ተጠቁሞ ነበር። በተጨማሪም ደረቅ የበጋ የአየር ጠባይ እንደሚያመዝን ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ሁኔታ ሊጠናከር እንደሚችል የበጋው ወቅት ከመጀመሩ በፊት መገለጹ የሚታወስ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለወቅቱ የተሰጠው ትንበያ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሞላጎደል ትክክለኛ መሆኑን ከግምገማው ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1ሐ)።

## 1.3 እ.ኤ.አ የ2022/23 የበጋ ወቅት በየክልሎች የነበረው ገፅታ

### 1.3.1 አፋር

የአፋር ክልል በበጋ ወቅት በአብዛኛው ደረቅ ሆኖ የሚቆይ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ግን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ይኖራል። በዘንድሮው በጋ በዞን 3፣4 እና 5 ከ50-150 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል አግኝቷ (ካርታ 1ሀ እና 1ለ) ። በክልሉ በዘንድሮው በጋ የጣለው ዝናብ በዞን አራት እና በጥቂት ዞን አምስት ከነበረው መደበኛ ዝናብ በስተቀር በተቀሩት ዞኖች ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደነበረ ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.2 ትግራይ

የትግራይ አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በበጋ ወቅት ደረቅ ሆነው የሚቆዩ ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ያገኛሉ። በአጠቃላይ በ2022/23 በጋ የክልሉ የምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅና ደቡባዊው ዞኖች ከ05-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ10-20 ለሚሆኑ ቀናት ነበራቸው (ካርታ 1ሀ እና 1ለ) ። በዚህም መሰረት ሁሉም የክልሉ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.3 አማራ

የክልሉ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በመደበኛ ሁኔታ እስከ ኦክቶበር መጨረሻ ድረስ ዝናብ ያገኛሉ። በክልሉ ምሥራቃዊ አጋማሽ የክረምቱ ዝናብ ቀደም ብሎ ከሴፕቴምበር አጋማሽ በኋላ የሚቋረጥበት አካባቢ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ በበጋ ወራት ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ያመዝንበታል። በዘንድሮው የበጋ ወቅት ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ባህርዳር ዙሪያ፣ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም ፣አዊ ዞኖች ከ50-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ10-35 ቀናት ያህል በማግኘት መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ እንዲሁም የተቀሩት የክልሉ ዞኖች ከ50-100 ሚ.ሜ ዝናብ ከ10-20 ቀናት ያህል በማግኘት ሁሉም የክልሉ ዞኖች ከመደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1ሀ ፣1ለ) እና 1ሐ) ።

### 1.3.4 ቤንሻንጉል ጉሙዝ

ቤንሻንጉል-ጉሙዝ በኦክቶበርና በኖቬምበር ወራት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚዘንብበት አካባቢ ነው። በዘንድሮው በጋ ወቅት በክልሉ በሚገኙ የመተከል፣ የአሶሳ እና የካማሺ ዞኖች ከ75-250ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ10-30 ቀናት ያህል አግኝተዋል (1ሀ እና 1ለ) ።በአጠቃላይ በሁሉም የክልሉ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደነበር መረዳት ይቻላል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.5 ጋምቤላ

የጋምቤላ ክልል በኦክቶበርና በኖቬምበር ወራት ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን፣በቀሪዎቹ ወራት ግን አብዛኛውን ጊዜ ደረቅ ሆኖ ቆይቷል።በክልሉ ምሥራቃዊ ክፍል የማጃንግ ዞን 250-350 ሚ.ሜ ለ30-40 ቀናት እንዲሁም የአኝዋክ ዞን ከ150-250 ሚ.ሜ ከ20-30 ቀናት ያህል አግኝተዋል። በተጨማሪም በክልሉ ምዕራብ የሚገኘው የኑዌር ዞን ለ11-25 ቀናት 100-200 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ (1ሀ እና 1ለ) ።በአጠቃላይ በክልሉ የዘነበው ዝናብ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ነበር (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.6 ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

በክልሉ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ እየተስፋፋ የሚሄደው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት ሲሆን፤ የክልሉ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ እንዲሁም ምዕራባዊ ክፍል በነዚህ ወራት የተሻለ ዝናብ ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል የክልሉ ሰሜናዊ ክፍል ከኦክቶበር በኋላ አልፎ አልፎ ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ከሚታይበት በስተቀር ብዙውን ጊዜ ደረቅ ሆኖ ይቆያል።በዘንድሮው በጋ ወቅት ክልሉ የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ የተስተዋለበት ሲሆን፤ በተለይም የክልሉ ምዕራብ ክፍል የሆኑት የቤንች ማጂ እንዲሁም አብዛኛው የወላይታ ዞን፤ ሰሜናዊ የሰገን ህዝቦች መጠኑ ከ150-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ30-40 ቀናት አግኝተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሀዲያና ጉራጌ፣ የደቡብ ኦሞ እንዲሁም አብዛኛው የሰገን ሕዝቦች ከ 50-200 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ከ11-30 ላልበለጡ ቀናት እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ(1ሀ እና 1ለ)።በዝናብ መጠን ረገድ በደቡባዊው ቤንች ማጂና ደቡብ ኦሞ ከተስተዋለው ከመደበኛ በታች ዝናብ በስተቀር የተቀሩት የክልሉ ዞኖች መደበኛ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1ሐ)።

### 1.3.7 ኦሮሚያ

የኦሮሚያ ምዕራባዊና ደቡባዊ አጋማሽ በኦክቶበርና በኖቬምበር የተስፋፋ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ የመካከለኛውና የምሥራቃዊ ክፍሎች ግን በኦክቶበር መጠነኛ ዝናብ ከሚኖራቸው በስተቀር በአብዛኛዎቹ የበጋ ወራት ደረቅ ሆነው ይቆያሉ። ይሁንና አልፎ አልፎ ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ለጥቂት ቀናት ያገኛሉ።

በዘንድሮው በጋ ወቅት ምሥራቅ ወለጋ፣ጅማ፣ኢሉአባቦራ፣ምዕራብ ወለጋ ከ150-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ30-58 ቀናት ያህል።በተጨማሪም ቦረናና ጉጂ፣ የባሌ እና የአርሲ ዞኖች ከ50-300 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ከ10-30 ቀናት ዝናብ ነበራቸው። በሌላ በኩል ምሥራቅ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ከ20-150 ሚ.ሜ ዝናብ ከ6-20 ቀናት ዝናብ ነበራቸው (1ሀ እና 1ለ) ። ምሥራቅ ወለጋ፣ጅማ፣ኢሉአባቦራ፣ምዕራብ ወለጋ ቦታዎችም የነበረው የዝናብ መጠን በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ የነበረ ሲሆን፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የአርሲና የባሌ እንዲሁም የቦረናና የጉጂ ሥፍራዎች ደግሞ ከመደበኛ በታች እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.8 ሶማሌ

ለሱማሌ ክልል ደቡባዊ አጋማሽ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅት በመሆኑ ለአርብቶ አደሩ ግጦሽና ለውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው። በበጋ ወቅት በተለይም በኦክቶበር በክልሉ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚገኝበት ጊዜ ሲሆን፣ ከኖቬምበር አጋማሽ በኋላ ግን ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ያመዝንበታል። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ዓመታት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ለተወሰኑ ቀናት ይኖራል።

በዘንድሮው በጋ በክልሉ የተለያየ መጠን ያለው የዝናብ ሁኔታ የተስተዋለበት ወቅት ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው የክልሉ ዞኖች ከ50-150ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ከ10-20 ባሉት ቀናት ውስጥ አግኝተዋል (1ሀ እና 1ለ) ።በዞኖቹ የነበረው የዝናብ መጠንም በአብዛኛው ከመደበኛው በታች ነበር (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.9 ሐረሪ

በሐረሪ ክልል በበጋ ወቅት መጀመሪያ ወር ላይ መጠነኛ ዝናብ የሚስተዋልበት ሲሆን፣ በቀሪዎቹ የበጋ ወራት ግን አልፎ አልፎ በአንዳንድ ዓመታት ከሚታየው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በስተቀር ብዙውን ጊዜ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ይቆያል። በመሆኑም በዘንድሮው በጋ በክልሉ 20-50 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ለ10-20 ቀናት ያህል ነበር (1ሀ እና 1ለ) ። በዚህም መሰረት በዘንድሮው በጋ በክልሉ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው በታች እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 1ሐ)።

### 1.3.10 ድሬዳዋ

በድሬደዋና አካባቢው በበጋ ወቅት ደረቅና ሞቃታማ የአየር ጠባይ የሚዘወተር ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ለጥቂት ቀናት ይዘንባል።በዘንድሮው የበጋ ወቅት በክልሉ 50-100 ሚ.ሜ መጠን ያለው ዝናብ ለ10-15 ቀናት አግኝቷል (1ሀ እና 1ለ)። በዚህም መሰረት የወቅቱ ዝናብ ከመደበኛ በታች እንደነበር መረዳት ይቻላል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.11 አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ አካባቢ በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የበጋ ወራት ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ እያመዘነ ሌሊትና ማለዳው ደግሞ ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ይስተዋልበታል። ነገር ግን በአንዳንድ ዓመታት ወቅታዊ ያልሆነ ዝናብ ይኖራል።

ባለፈው በጋ 2022/23 በአዲስ አበባና አካባቢው 25-50 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ነበር (1ሀ እና 1ለ) ። የዘነበው የዝናብ መጠንም ከመደበኛው በታች እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.12 ደቡብ ምዕራብ

በክልሉ ዞኖቸ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ እየተስፋፋ የሚሄደው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት ሲሆን፣ የክልሉ ምዕራባዊ ክፍል በእነዚህ ወራት የተሻለ ዝናብ ይኖራቸዋል። በዘንድሮው በጋ ወቅት በክልሉ የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ የተስተዋለበት ሲሆን፤ በተለይም የክልሉ ምዕራብ ክፍል የሆኑት የሸካ ፣የከፋ እንዲሁም አብዛኛው የኮንታ ዞን መጠኑ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ30-58 ቀናት ማግኘታቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ (1ሀ እና 1ለ) ። የዘነበው የዝናብ መጠንም መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1ሐ) ።

### 1.3.13 ሲዳማ

በክልሉ ዞኖቸ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ እየተስፋፋ የሚሄደው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት ሲሆን፣ የክልሉ ደቡብ ምስራቅ ክፍል በእነዚህ ወራት የተሻለ ዝናብ ይኖራቸዋል። በዘንድሮው በጋ ወቅት ክልሉ የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ የተስተዋለበት ሲሆን! በተለይም የክልሉ ደቡባዊ ክፍል የዝናብ መጠኑ ከ150-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ30-40 ቀናት ማግኘታቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ (1ሀ እና 1ለ) ። የዘነበው የዝናብ መጠንም በአመዛኙ መደበኛ የሆነ ዝናብ እንደነበር ከተጠናቀሩ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1ሐ) ።

## ምዕራፍ ሁለት

# 2.0 እ.ኤ.አ የ2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## 2.1 መግቢያ

በልግ ከፌብርዋሪ እስከ ሜይ ድረስ ያሉትን ወራት ያካትታል። ይህ ወቅት ለደቡብና ለደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ዋነኛው የዝናብ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት የሚኖረው ዝናብ አጀማመሩ ከዓመት ዓመት ከፍተኛ ተለዋዋጭነት የሚያሳይ ቢሆንም፤ በመደበኛ ሁኔታ ግን ከፌብርዋሪ አጋማሽ በኋላ መዝነብ ይጀምራል። የወቅቱ ዝናብ በመደበኛው ሁኔታ ተስፋፍቶ መዝነብ የሚጀምረው ግን ከማርች የመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ በመሆኑ ከማርች አጋማሽ እስከ ኤፕሪል መጨረሻ ድረስ ያሉት ወሳኝ የዝናብ ጊዜያት ናቸው። በዚህ ፅሁፍ በበልግ ወቅት በመደበኛው ሁኔታ በሚስተዋሉት የአየር ጠባይ ክስተቶች ላይ ትንታኔ በመስጠት የመጪው በልግ የአየር ጠባይ አዝማሚያ ይጠቆማል። በመጨረሻም በወቅቱ ውስጥ ከሚጠበቀው የአየር ጠባይ ጋር በተገናዘበ መልኩ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ በተመለከተ ማብራሪያ ይቀርባል።

## 2.2 የበልግ ወቅት የዝናብ አማካይ ገጽታ

የበልግ ዝናብ በአጀማመሩም ሆነ በአወጣጥ ረገድ ከፍተኛ ተለዋዋጭነት የሚያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ በመጠንና በስርጭትም የተለዋዋጭነት ባህሪይ ያሳያል። በዚህም መሠረት በበልግ ወቅት በእያንዳንዱ ወር በመደበኛው ሁኔታ የሚኖረው የዝናብ ሁኔታን ማወቁ ለወቅቱ የተሰጠውን ትንበያ በጥንቃቄ ለመጠቀም ይረዳል።

በፌብርዋሪ በመደበኛው ሁኔታ የሚታየው የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በልግ አብቃይ አካባቢዎች፣ በጅማ፣ በቦረና፣ በጉጂ፣ በሰሜን ሸዋና ወሎ አንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከ21-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና የሱማሌ ደቡባዊ አጋማሽና አጎራባች የኦሮሚያ ደቡባዊ ክፍል አካባቢዎች በዚህ ወር ብዙውን ጊዜ ደረቅ ሆነው ስለሚቆዩ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ10ሚ.ሜ አይበልጥም (ካርታ 2ሀ እና 4ሀ) ።

በማርች የበልግ ዝናብ ቀስ በቀስ በሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ ከመሄድ አንፃር የተሻለ ዝናብ ይስተዋላል። ስለሆነም በዚህ ወር ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በልግ አብቃዮች መካከል የጌድኦ ዞን፤ የሲዳማ ክልልና አጎራባች አካባቢዎችን ጨምሮ የምዕራብ ኦሮሚያ አንዳንድ ቦታዎች ከ50-100ሚ.ሜ ዝናብ ከ10-15 ቀናት ያህል ይኖራል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ የወሎ፣ የአርሲና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ደቡባዊ ክፍል ከ50-150ሚ.ሜ ዝናብ ከ10-20 ቀናት ያህል ያገኛሉ። ከሱማሌ ክልል ዋነኛ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆነው በደቡባዊ አጋማሽ አካባቢ ላይ የዝናቡ ሁኔታ ከቀዳሚው ወር እየተሻሻለ የሚመጣ ቢሆንም መጠኑ ከ70ሚ.ሜ የማይበልጥ ሆኖ ከ10 ለማይበልጡ ቀናት በአማካይ ይዘንባል (ካርታ 2ለ እና 4ለ) ።

ከበልግ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በኤፕሪል የሚዘነበው ዝናብ ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን የደቡብ ትግራይና የሱማሌ አካባቢዎችን ጨምሮ በተቀሩት የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከ50-100 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ10-20 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ለ10 ቀናት ያህል እስከ 100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና የደቡብ ኦሮሚያ 150-250ሚ.ሜ ለ20 ቀናት ይደረሳል (ካርታ 2ሐ እና 4ሐ) ።

የበልግ ወቅት መጨረሻ በሆነው በሜይ የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ ከመሄዱም በተጨማሪ ከመካከለኛው፤ ከምሥራቅና ከሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያም ይቀንሳል። ነገር ግን ዝናቡ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ በመሄድ ብዙ ቦታዎችን ያዳርሳል። በዚህም መሠረት አብዛኛው የኦሮሚያ ክልልን ጨምሮ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልልና የጋምቤላ አካባቢዎች ከ150-250 ሚ.ሜ ዝናብ ከ15-25 ቀናት ያህል ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይና የአማራ ምዕራባዊ ክፍልና የሱማሌ አካባቢዎች እስከ 100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ለ10-15 ቀናት ያህል በአማካይ ያገኛሉ (ካርታ 2መ እና 4መ)።

ጠቅለል ባለ መልኩ የበልግ ወቅት ዝናብ በአማካይ በሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረው ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ይልቅ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በምዕራብ፣ በምሥራቅና በደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ ከ300-600 ሚ.ሜ

ይደርሳል። ይሁንና ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በተቀሩት የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አከባቢዎች ላይ ይስተዋላል። በሌላ በኩል ደግሞ የአፋር፣ የትግራይና አጎራባች የአማራ ምዕራባዊ ክፍል አካባቢዎች እስከ 150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ያገኛሉ (ካርታ 2ሠ) ።

## 2.3 የበልግ ወቅት የዝናብ ድርሻ

የበልግ ወቅት ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በአንድ በኩል ከሀገሪቱ አጠቃላይ የዝናብ ድርሻ ከክረምት ቀጥሎ ሁለተኛው የዝናብ ወቅት ሲሆን፤ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ደግሞ ዋነኛው የዝናብ ወቅት ነው። በዚህም መሠረት በዚህ ወቅት በመደበኛው ሁኔታ የሚኖረው የዝናብ መጠንና ሥርጭት ከአማካይ ዓመታዊ ዝናብ መጠን ጋር ሲነፃፀር ያለው ድርሻ እንደየአካባቢው ሁኔታ ይለያያል። ለምሳሌ ያህል በበልግ ወቅት በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በአማካይ የሚኖረው የዝናብ መጠን በዓመት ውስጥ ማግኘት ከሚገባቸው ከ60% በላይ የሚደርስ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ደግሞ ከ30-40% ይደርሳል። ከኤፕሪል አጋማሽ በኋላ ቀስ በቀስ ዝናብ እየተስፋፋ በሚሄድባቸው ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ደግሞ የበልግ ዝናብ ድርሻ በአማካይ ከ20% አይበልጥም። ስለሆነም የበልግ ወቅት ዝናብ ምንም እንኳን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚካሄዱት የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በጣም አስፈላጊ ቢሆንም በዋነኛ የበልግ አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚካሄዱት የእርሻ ሥራም ሆነ ለአርብቶ አደሩ የውሃና ግጦሽ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (ካርታ 3ሠ) ።

## 2.5 በበልግ ወቅት የሚስተዋለው የሙቀት ሁኔታ

በበልግ ወቅት በመደበኛው ሁኔታ ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። ይህም ሲባል በበልግ ወቅት በመደበኛው ሁኔታ ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑና የሌሊቱ የሙቀት መጠን እየጨመረ የሚሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ በወይና ደጋና ቆላማ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሌሎች አካባቢዎች በተለየ መልኩ የመጨመር አዝማሚያ ያሳያል። በመሆኑም በአፋር፣ በሶማሌ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ ቆላማ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት አልፎ አልፎ ከ40 ዲ.ሴ. በላይ ይሆናል።

በተጨማሪ በትግራይ ምዕራባዊ ክፍል፣ በምሥራቅ አማራ፣ በኦሮሚያ የስምጥ ሸለቆ አካባቢዎችና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደቡባዊ ክፍል የተለያዩ ቦታዎች በመደበኛው ሁኔታ የሚኖረው የቀኑ ሙቀት ከ35-40 ዲ.ሴ. ይደርሳል። ስለሆነም ተጠቃሚዎች ለወቅቱ የተሰጠውን ትንበያ ከአማካይ የአየር ጠባይ ጋር በማነፃፀር ሊጠቀሙበት ይገባል።

## 2.6. እ.ኤ.አ 2022/23 በልግ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ አሰጣጥ

ለዘንድሮ የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የበልግ ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ጥናት የተደረገ ሲሆን፣ መጪው የበልግ ወራት የምስራቅና የመካከለኛዉ ፓስፊክ ዉቅያኖስ የላይኛዉ የውሃ አካላት የበልግ ወራት ወደ መደበኛው ሁኔታ ጋር የተቀራረበ (ENSO-neutral) የመሄድ ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ የትንበያ መረጃዎች ያስረዳሉ። በአሁኑ ወቅት የመካከለኛው ፓሰፊክ ውቂያኖስ በLanina ክስተት ተጽዕኖ ሥር ያለ ሲሆን፤ በሂደትም ወደ መደበኛ ሁኔታ (ENSO-neutral) የመሆን ዕድሉም ከ82-85% እንደሆነ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ። በተጨማሪም የሰሜናዊ ህንድ ዉቅያኖስ ምዕራባዊ ክፍሉ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ በተመሳሳይ ደግሞ ምስራቃዊ ክፍሉ ከመደበኛው የቅዝቃዜ ሁኔታ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘንድሮ የበልግ ወቅት (Neutral-IOD) ስር ሊሆን እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም ከሰሜን ህንድ ዉቅያኖስ ወደ ሀገራችን ሊገባ የሚችለዉ እርጥበት አዘል አየር ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ሊኖረው እንደሚችል በባለሙያዎች ትንታኔ ተመላክቷል።

በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ ከ1981 ጀምሮ ከታዩት የኤልኒኖ/ላኒና ወይም መደበኛ ክስተቶች መካከል እ.ኤ.አ 2001፣ 2006 እና 2021 ተመሳሳይ ዓመታት ተመርጠዋል። በአጠቃላይ የበልግ ዝናብ በአብዛኛው በቦታና በጊዜ በሚያሳየው ወጥ ያልሆነና ከፍተኛ መዋዠቅ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ወራት ደረቃማ ቀናት ሊዘወተሩ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በመጪው እ.ኤ.አ 2023 የበልግ ወራት፣ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ለደቡብና ለአብዛኛው የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የሰሜን ምስራቅ፤ የመካከለኛውና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

በተጨማሪም የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ግንዛቤ ተወስዷል።

የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛው በላይ ሊሞቅ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። በአጠቃላይ በመጪው የበልግ ወቅት በአብዛኛው ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የመሆን ዕድሉ ሰፊ እንደሚሆን ይጠበቃል።

## 2.6. እ.ኤ.አ የ2022/23 በጋ ወቅት በክልሎች የሚጠበቅ የአየር ጠባይ አዝማሚያ

### 2.6.1. አፋር

በአፋር ሰሜንና ምሥራቅ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ሙቀት የሚያመዝንበት በመሆኑ በበረሃማነቱ ይታወቃል። ነገር ግን በበልግ ወቅት አልፎ አልፎ ከተጠናከረ የዝናብ ሰጪ ክስተቶች የክልሉ ምዕራባዊ ዳርቻዎችና ደቡባዊ ክፍሉ መጠነኛ ዝናብ ያገኛሉ። በዚህ ወቅት በክልሉ አብዛኛው ክፍል ላይ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው ዝናብ ከአካባቢያዊ የመሬት አቀማመጥ ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ደረጃ የመዋዠቅ ባህሪይ ያሳያል (ካርታ 2ሀ-ሠ) ።

በመጪው የበልግ ወቅት በሁሉም የክልሉ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአብዛኛው ደረቅና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝንባቸው ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

### 2.6.2. ትግራይ

የትግራይ ክልል ደቡባዊ ክፍሉ በበልግ አብቃይነቱ የሚታወቅ በመሆኑ በበልግ ወቅት የሚያገኘው ዝናብ ለእርሻ ሥራ ተፈላጊ ነው። ምንም እንኳን በዚህ አካባቢ በመደበኛው ሁኔታ ዝናብ ከማርች እስከ ሜይ መግቢያ ድረስ ዝናብ የሚጠበቅ ቢሆንም የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከፍተኛ የመዛባት ባህርይ ያሳያል (ካርታ 2ሀ-ሠ) ።

በመጪው በልግ የክልሉ በልግ አብቃይ አካባቢዎች የሆኑት የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፣ የመካከለኛና የምዕራባዊው ክፍል ዞኖችን ጨምሮ በአብዛኛው ከመደበኛው በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 5) ።

### 2.6.3 አማራ

የአማራ ክልል ምሥራቃዊ አጋማሽ በበልግ አብቃይነቱ የሚታወቅ በመሆኑ በበልግ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛል። በተለይም በዚህ አካባቢ ላይ አልፎ አልፎ

ዝናብ ሰጪ ክስተቶች ሲጠናከሩ ከበድ ያለ ዝናብ ይስተዋላል። በበልግ ወቅት የሚኖረው አማካይ የዝናብ መጠን በሰሜን ሸዋ፣ በኦሮሚያ ለዩ ዞን እና በወሎ ዞኖች ላይ ከፍተኛ ሲሆን፣ የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በክልሉ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ በጎላ መልኩ እየቀነሰ ይሄዳል። በተለይም በክልሉ ሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ እስከ በልግ አጋማሽ ድረስ አመዝኖ የሚቆይ ሲሆን፣ ከኤፕሪል አጋማሽ በኋላ ዝናቡ ቀስ በቀስ መዝነብ ይጀምራል (ካርታ 2ሀ-ሠ) ።

በመጪው በልግ በክልሉ በልግ አብቃይ አካባቢዎች በሆኑት ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ዋግ ህምራ፣ የኦሮሚያ ለዩ ዞን፣ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ምሥራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

### 2.6.4. ቤንሻንጉል ጉሙዝ

ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ክፍሉ ከማርች አጋማሽ ጀምሮ በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ ማግኘት የሚጀምር ሲሆን፣ የሰሜን ምዕራብ ቆላማ ክፍሉ ግን ከክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች መጠናከር ጋር በተያያዘ ከኤፕሪል አጋማሽ በኋላ ቀስ በቀስ ዝናብ ማግኘት ይጀምራል (ካርታ 2ሀ-ሠ) ። በተለይም በዚህ ወቅት በክልሉ ቆላማ አካባቢ ላይ በመደበኛው ሁኔታ የሚኖረው ሙቀት በጣም ከፍተኛ ነው።

በመጪው በልግ በአብዛኛው የክልሉ አካባቢ ላይ ዝናብ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ ሁሉም የክልሉ ዞኖች (የአሶሳ፣ የካማሺና የመተከል ዞኖች) በመጠን ረገድ በአመዛኙ መደበኛ እና በጥቂት ኪስ ቦታዎች ደግሞ ከመደበኛው በላይ ዝናብ ያገኛል (ካርታ 5) ።

### 2.6.5 ጋምቤላ

የጋምቤላ ክልል በበልግ ወቅት ከፍተኛ የሙቀት መጠን የሚስተዋልበት ቢሆንም እንደሌሎች የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ሁሉ በዚህ ወቅት ዝናብ ከሚያገኙት ውስጥ ይመደባል። ይሁንና መደበኛው የወቅቱ ዝናብ በአብዛኛው በክልሉ ምሥራቃዊ አጋማሽ ላይ የተሻለ የቦታ ሽፋንና መጠን አለው (ካርታ 2ሀ-መ) ።

በመጪው በልግ በአብዛኛው የክልሉ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የበልግ ዝናብ ይጠበቃል።ዝናቡ በአጀማመርም ሆነ በአወጣጥ መደበኛውን ፈር እንደሚከተል ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

## 2.6.6 ኦሮሚያ

በኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የጉጂ፣ የባሌ፣ የአርሲ፣ የምሥራቅ ሸዋና የሐረርጌ አካባቢዎች የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች ሲሆኑ፤ በተለይም በቦረና፣ በጉጂና በባሌ ቆላማ አካባቢዎች ላይ በበልግ ወቅት የሚጥለው ዝናብ ከፍተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ስርጭቱም ሰፊ ቦታን የሸፈነ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ምዕራባዊ ክፍል በዚህ ወቅት በመደበኛው ሁኔታ ዝናብ ያገኛል። የክልሉ ማዕከላዊ ክፍልን በተመለከተ ደግሞ ምንም እንኳን ከወቅቱ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ማግኘት የሚጀምር ቢሆንም በመጀመሪያዎቹ የበልግ ወራት አነስተኛ ዝናብ ያገኛል (ካርታ 3ሀ-ረ) ።

በመጪው በልግ በጅማ፣ በኢሉአባቦራ፣የቦረናና የጉጂ፣ ፣ የምዕራብና ሰሜን ሸዋ ፣ የምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ በአብዛኛው መደበኛና ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ደግሞ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተጨማሪም የምዕራብ እና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ የምዕራብ ሸዋ፣ የባሌና የአርሲ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን እንደሚያገኙ ሲጠበቅ በአንዳንድ ቦታዎቻቸውም ላይ ከመደበኛ በታች ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 5) ።

## 2.6.7. ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

የክልሉ አብዛኛው ክፍል በበልግ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ ያገኛል። በተለይም ዝናቡ በክልሉ ምዕራባዊና ደቡባዊ አጋማሽ ክፍሎች ላይ የተጠናከረ ገፅታ የሚኖረው ሲሆን፤ በሰሜን የክልሉ ዳርቻዎች ላይ ግን ከክረምት ወቅት ጋር የተያያዘ በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይቆያሉ። በተለይም በክልሉ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ላይ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅት በመሆኑ የዝናብ መጠንና ሥርጭትም በዚያው መልክ የተሻለ ገፅታ አለው (ካርታ 3ሀ-ረ) ።

በመጪው በልግ በክልሉ የሚገኙት ሁሉም ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛው በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸውም ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል በተጨማሪም ዝናቡ በአጀማመር ሆነ በአወጣጥ መደበኛውን ፊር እንደሚከተል ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

### 2.6.8. ሶማሌ

የሶማሌ ክልል አብዛኛው ክፍል (ከሰሜን ዳርቻዎች በስተቀር) የበልግ ወቅት ዝናብ ያገኛል። ነገር ግን የክልሉ ደቡባዊ አጋማሽ በዚህ ወቅት ከቀሪዎቹ ወቅቶች ጋር ሲነፃጸር ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረዋል። በመደበኛው ሁኔታ በዚህ አካባቢ ላይ የበልግ ዝናብ ከማርች አጋማሽ ጀምሮ መጣል የሚጀምር ሲሆን፤ በኤፕሪል ሰፊውን ቦታ የሸፈነ ዝናብ ይኖራል። ዝናቡ ከሜይ መግቢያ ጀምሮ በመቀነስ ቀስ በቀስ በደረቅ ሁኔታ ይተካል። የወቅቱ ዝናብ ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ተለዋዋጭነት የሚያሳይ ቢሆንም በበልግ ወቅት የሚኖረው ዝናብ ከዓመቱ አማካይ ዝናብ ከ50-70% ያህሉን ስለሚሸፍን ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት መስተካከል ለአርብቶ አደሩ ውሃና ግጦሽ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ሰሜናዊ አጋማሽ አልፎ አልፎ ዝናብ የሚያገኝ ቢሆንም የዝናቡ መጠንና ስርጭት እንደ ክልሉ ደቡባዊ ክፍል የተጠናከረ አይሆንም (ካርታ 3ሀ-ረ)።

በመጪው በልግ በክልሉ የሚገኙት የሊበን፣ የአፍዴር፣ የጎዴ፣ ቆራሄና ዋርዴር በአመዛኙ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። ፊቅና ዱጋሃቡር ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሲቲ እና የጅግጅጋ ዞኖች (ካርታ 5) ።

### 2.6.9 አዲስ አበባ

አዲስ አበባና አካባቢው ብዙውን ጊዜ ዝናብ ሰጪ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከደቡብ ወደ ሰሜን በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወይም በስምጥ ሸለቆ አጎራባች ደጋማ ስፍራዎች ላይ ምቹ ሆነው ሲገኙ የተስፋፋ ዝናብ ያገኛል። በፌብርዋሪ በመደበኛው ሁኔታ ደረቅ ሆነው የሚቆይ ቢሆንም በማርችና በኤፕሪል ወራት ግን የተሻለ ዝናብ ይኖረዋል (ካርታ 3ሀ-ረ) ።

በመጪው በልግ በአዲስ አበባና አካባቢው ላይ በጊዜና በቦታ የመዋዠቅ ባህሪይ ያለው የበልግ ዝናብ እንደሚኖርና በመጠን ረገድም በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የመኖር ዕድሉ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

### 2.6.10 ድሬዳዋ

በድሬደዋ አካባቢ በበልግ ወቅት አልፎ አልፎ ዝናብ የሚኖር ቢሆንም የሚዘንብባቸው ቀናት ብዛት ከአጎራባች ምሥራቅ ኦሮሚያ አካባቢዎች ያንሳል። ይሁንና በማርችና በኤፕሪል ወራት ከቀሪዎቹ የበልግ ወራት የተሻለ ዝናብ በአማካይ ይኖረዋል (ካርታ 3ሀ-ረ) ።

በመጪው በልግ በድሬደዋ አካባቢ ላይ የሚኖረው ዝናብ በቦታና በጊዜ ስርጭት አንፃር የመዋዠቅ አዝማሚያ ያሳያል። በመጠን ረገድም ቢሆን የወቅቱ ዝናብ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የመሆን ዕድሉ ከፍ ያለ ይሆናል (ካርታ 5) ።

### 2.6.11. ሐረሪ

በሐረሪ ክልል የበልግ ዝናብ በመደበኛው ሁኔታ የሚዘንብ ቢሆንም የተስፋፋ መልክ የሚኖረው ከማርች አጋማሽ ጀምሮ እስከ ሜይ መጀመሪያ ድረስ ባሉት ጊዜያት ነው። ይሁንና በዚህ ክልል ላይ የወቅቱ ዝናብ በሌሎች የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች እንደሚታየው ዓይነት የተጠናከረና የተስፋፋ መልክ አይኖረውም። ስለሆነም በወቅቱ ውስጥ የዝናቡ መጠንና ሥርጭት የመዋዠቅ ባህሪይ በጎላ መልኩ ይታይበታል (ካርታ 3ሀ-ረ) ።

በመጪው በልግ በክልሉ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ይጠበቃል (ካርታ 5) ።

### 2.6.12. ሲዳማ


ክልሉ በበግል ወቅት አብዛኛው ክፍል በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ ያገኛል። በተለይም በክልሉ ምዕራብና ደቡባዊ አጋማሽ አካባቢዎች ላይ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በመሆኑ የዝናብ መጠንና ሥርጭትም በዚያው መልክ የተሻለ ገፅታ አለው (ካርታ 3ሀ-ረ)።

በመጪው የበልግ ወቅት የክልሉ የሰሜን እና የምዕራብ አጋማሽ አብዛኛዉ ክፍል መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ቦታዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደሚያገኝ ይጠበቃል (ካርታ 5)


### 2.6.13. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

የክልሉ አብዛኛው ክፍል በበልግ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ ያገኛል። በተለይም ዝናቡ በክልሉ ደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ላይ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅት በመሆኑ የዝናብ መጠንና ሥርጭትም የተጠናከረ ገፅታ የሚኖረው ሲሆን፤ በሰሜን እና በሰሜን ምዕራብ የክልሉ ክፍሉ ግን ከክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች መጠናከር ጋር በተያያዘ ከማርች አጋማሽ በኋላ ቀስ በቀስ ዝናብ ማግኘት ይጀምራ (ካርታ 3ሀ-ረ) ።


በመጪው በልግ በአብዛኛው የክልሉ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የበልግ ዝናብ ይጠበቃል። ዝናቡ በአጀማመር ሆነ በአወጣጥ መደበኛውን ፈር እንደሚከተል ይጠበቃል (ካርታ 5)።





ካርታ 1ሀ. እ.ኤ.አ 2022/23 የበጋ ወቅት የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 1ለ. እ.ኤ.አ 2022/23 በበጋ ወቅት የነበረው ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት





ካርታ 1ሐ. እ.ኤ.አ 2022/23 የበጋ ወቅት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር።





ካርታ 2ሀ-መ የፌብርዋሪ፣ የማርች፣ የኤፕሪል እና የሜይ አማካይ የዝናብ መጠን (በሚ.ሜ)





ካርታ 2ሠ የበልግ ወቅት አማካይ የዝናብ መጠን (በሚ.ሜ)




ካርታ 3ሀ-መ የበልግ ወቅት የወራት አማካይ የዝናብ የዝናብ ድርሻ (በፐርሰንት)





ካርታ 3ሠ የበልግ ወቅት አማካይ የዝናብ ድርሻ (በፐርሰንት)




ካርታ4ሀ-ሠ የበልግ ጠቅት የጠሩት የዝናብ ቀናት እና የበልግ ጠቀት የዝናብ ቀናት

## የአየር ጠባይ: እ.ኤ.አ 2023 የበልግ ወቅት የዝናብ ትንበያ




ካርታ 5) እ.ኤ.አ በ2023 የበልግ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው የዝናብ መጠን በመደበኛ ሁኔታ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ጋር በማነፃፀር የመኖር ዕድሉ በመቶኛ

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 እ.ኤ.አ የበጋ 2022/23 ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በበጋ ውቅት የሚኖረው ምቹ የአየር ፀባይ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የመኸር አብቃይ በሆኑ አከባቢዎች የተለያዩ ሰብሎቹ እድገታቸውን የሚጨርሱበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚካሄድበት ጊዜ ሲሆን በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የአርብቶ አደሩና ከፊል አረብቶ አደር አከባቢዎች ለግጦሽና ለመጠጥ ውሀ እንዲሁም መጠነኛ የሆነ እርሻ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ጊዜ ነው።

እ.ኤ.አ የኦክቶበር ወር 2022 በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በመድረቅ ሂደትና በመሰብሰብ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ ሆኖም ግን ለእርጥበት መጨመር ምቹ ከነበረው የሚቲዎሮሎጂ ክስተት መጠናከር ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ በተጨማሪም የመካከለኛው ኦሮሚያ፣ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከእርጥበታማ እስከ እጅግ በጣም እርጥበታማ (Moist to Hyper-humid) እርጥበት ይዘት እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ተጠናክሮ የታየው እርጥበታማ ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እድገት የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት ከማስገኘት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበርው። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተለያዩ የግብርና እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልም ገንቢ ሚና ነበረው። ሆኖም ግን በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ የእርጥበት መጠኑም እየተሰፋፋ እነደሄደ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች ላይ አሉታው ተፅእኖ የማስከተል አቅም ቢኖረውም የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ ግን የቀረበ ሪፖሪት የለም። ነገር ግን የተገኘው ከፍተኛ

መጠን ያለው እርጥበት ውሃ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረ ነበር፡፡

እ.ኤ.አ የኖቬምበር ወር 2022 በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡ ፡ በአንፃሩም ከደረቃማው የአየር ሁኔታና ከደመና ሽፋን መሳሳት ጋር ተዳምሮ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በተለይም ከሁለተኛዉ አስር ቀን ጀምሮ በአንፃራዊ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበረ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፤ በተለይም በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በተከታታይ ቀናት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ ቅዝቃዜ መቋቋም በማይችሉና ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎች የጓሮ አትክልቶችና በተለያዩ የፍራፍሬ ተክሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን  አሉታዊ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም ነበረው፡፡ በሌላም በኩል የበጋው ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ  ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የተገኘው እርጥበት የጎላ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘዉ  እርጥበት  በደጋማው አካባቢ ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋጽዕ ነበረው። በተጨማሪም ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ ከነበረው የደመና ክምችት ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣  በምዕራብ እና በደቡብ ምስራቅ  በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የተገኘዉ ከባድ ዝናብ በተወሰነ ቦታዎች በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች ላይ አሉታው ተፅእኖ ቢኖረውም ውሃ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረ ነበር፡፡


እ.ኤ.አ በዲሴምበር ወር 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በተለይም ከግብርና የስራ እንቅስቃሴ አንጻር ሰብል ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ

ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በተጨማሪም የለሊትና የማለዳዉም ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሰሜን፣ መካከለኛው፣ ደቡብና ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ባልደረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙና ቅዝቃዜ በማይቋቋሙ አንዳንድ ሰብሎች የጓሮ አትክልቶችና የፍራፈሬ ተከሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ በዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አንፃራዊ የሆነ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ስለነበር የለሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ጋብ ብሎ ተስተዉሏል፡፡ በሌላ በኩል ከነበረዉ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በመኖሩ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የእርጥበታማ ሁኔታው በአመዛኙ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ ለሚዘሩ ሰብሎች ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም፤ በአንዳንድ ስፍራዎች በደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ባሉ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችልበት እድል ነበረው፡፡

እ.ኤ.አ የጃንዋሪ ወር 2023 የበጋው ደረቃማ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በወቅቱ እየተከናወነ ካለው የግብርና እንቅስቃሴ አንፃር በጎ ጎን ነበረው፡፡ በመሆኑም በወሩ ውስጥ የተስተዋለው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች እንዲደርቁ፤ በጊዜ እንዲሰበሰቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዜሮ ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል በደብረብርሀን -1.2፣ -0.8፣ በሐሮማያ -1.4፣ -1.2፣ -0.6 -0.2፣ እንዲሁም በመሐል ሜዳ -1.5 እና 0.0 ዲግሪ ሴልሽየስ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የተስተዋለው ቅዝቃዜ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙና ቅዝቃዜ በማይቋቋሙ አንዳንድ ሰብሎች በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይም ሆነ በእንስሳት ሁለንተናዊ ጤንነት ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም ነበረው። ይሁንና አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን በምእራብ አጋማሽ፣ በምስራቅ፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ መጠን ያለዉ እርጥበት ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ለደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ለነበሩ ሰብሎች በጥቂት ቦታዎች

አሉታዊ ጎን የነበረው ቢሆንም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑትም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለአትክልቶችና ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው።

በአጠቃላይ ባሳለፍነው 2022/23 የበጋ ወራት የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በተለይም የክረምት ዝናብ ሰጪ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታ ቶሎ ካለመዳከሙ ጋር ተያይዞ የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ በአወጣጥ ረገድ በተወሰነ ደረጃ የቆየበትና በተጨማሪም የበጋ ወቅት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት (ጥቅምት እና ህዳር) በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት እንደነበረ ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በነዚህ አካባቢዎች ዘግይተው ለተዘሩ እድገታቸውን ላልጨረሱና ተጨማሪ እርጥበት ለማያስፈልጋቸው ሰብሎች ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በጎ ጎን ነበረው። በአንፃሩም የበጋው ወቅት ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ደረቅ፤ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ከመቆየቱ ጋር የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ይሁን እንጂ በተለይም በወቅቱ መገባደጃ በነበሩት ሁለት ወራት የነበረው ቅዝቃዜ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ በሰሜን፤ በሰሜን ምስራቅ፤ በምስራቅ፤ በመካከለኛዉና በደቡብ ከፍተኛ ቦታዎች ዝቅተኛው የሙቀት መጠን ከ$5^{\circ}C$ በታች ሆኖ የተመዘገበትና እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎችም ከ ዜሮ $^{\circ}C$ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ባልደረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች በመስኖ በሚለሙ የጓሮ አትክልቶችና የፍራፍሬ ተክሎች እና በእንሰሳ ጤና ላይ በመጠኑም ቢሆን የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ የማሳደር ጥንካሬ ነበረው፡፡ በአጠቃላይ ባለፈው የበጋ ወቅት በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው፣ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆነው (Hageya/Deyr) ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚገባቸው በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በተለይም በቦረና፣ ጉጂና በባሌ ቆላማ ኪስ ቦታዎች የእርጥበት ሁኔታ አመላካች (Moisture Index), ከሳተላይት የሚሰበሰበው የእፅዋትን ሽፋን አመላካች (NDVI) እንዲሁም በአረብቶ አደሩ አከባቢ የሚሰላው (Rangeland WRSI) የሚጠቁመው መረጃ እንደሚያሳየው የእርጥበት እጥረት ታይቶባቸው ነበር። በዚሁ የተነሳም የእንስሳት መኖም ሆነ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ እጥረት እንደነበርና የምግብ ዋስትናቸውም ዝቅተኛ እንደነበረ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 3.1) ያሳያል።





ካርታ 3.1፡ በበጋ 2022/23 በየወሩ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በቦታ ሽፋን

## 3.2 እ.ኤ.አ በ2022/23 የበጋ ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በዉሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረዉ ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው አራት የበጋ ወራት የነበረውን የእርጥበት ሁኔታ ስንመለከት በኦክቶበር ወር ከተገኘው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ እንደነበረ የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን በኦክቶበር ወር በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣የላይኛው እና መካከለኛ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤሸበሌ መካከለኛው ተከዜ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ እርጥበት አግኝተዋል።በዚህ ወር የተገኘው እርጥበት የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው አዎንታዊ አስተዋፅዎ ነበረው። እንዲሁም በኖቬምበር ወር የነበረውን የእርጥበት ሁኔታ ስንመለከት በመጠንም ሆነ በስርጭት በጥቅምት

ወር ከተገኘው የቀነሰ እንደነበረ የታየ ሲሆን፤ ሆኖም ጥቂት ተፋሰሶች ማለትም በላይኛው እና መካከለኛው የባሮ አኮቦ፣ መካከለኛው እና የታችኛው የኦሞ ጊቤ፣ በጥቂት የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ እና የአባይ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው። በአንጻሩ በዲሴምበር እና በጃንዋሪ ወር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን በመጨረሻ የዲሴምበር አስር ቀናት በተለይም የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው የኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው።

በአጠቃላይ ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ በነበሩት ወራት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች በበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር የነበሩ ሲሆን ነገር ግን በመጀመሪያዎቹ የበጋ አጋማሽ ወራት (በኦክቶበር እና በኖቬምበር) እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኙ ተፋሰሶች እንደነበሩ መረጃዎች ያመለከቱ ሲሆን ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጉ ከመልካ ዋከና እና ቆቃ ግድብ በስተቀር በሁሉም ግድቦችና ውሃ ማጠራቀሚያዎች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የውሃ መጠን እንደነበራቸው የተመዘገቡ የግድብ ከፊታ መረጃዎች ያመላክታል (ካርታ 3.2) ፡፡





ካርታ 3.2: በበጋ 2022/23 በየወሩ የነበረው የተፋሰሶች እርጥበት ሁኔታ

Weather: ዝናብ፣ሙቀት እና ምዝን የአየር እርጥበት

## 3.3 የበጋ 2022/23 ወቅት የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

የበጋ 2022/23 ወቅት ግምገማ በዋናነት ሶስቱን ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ማለትም ወርሃዊ የዝናብ መጠን፣ የምዝን አየር እርጥበትና ወርሃዊ አማካይ የሙቀት መጠን መሠረት በማድረግ ሲሆን ለወባ ትንኝ መፈጠር ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችንና ለሰው ልጅ ተስማሚ (ምቹ) የአየር ሁኔታ ያለባቸው ቦታዎችን መጠቆም ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የዘንድሮ በጋ 2022/23 ወቅት ስንመለከት በተለይም በኦክቶበር ወር የነበረው የዝናብ፣ ሙቀትና የአየር እርጥበት በአብዛኛው የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው የደቡብና የምስራቅ ጫፍ የሀገሪቱ ክፍሎች ለወባ ትንኝ መራባትና መፈጠር አመቺ የሚቲዎሮሎጂ ሁኔታዎች የነበሩ ሲሆን ለመጥቀሰም ያህል ሰሜን ጎንደር፣አዊ፣ባህር ዳር ዙሪያ፣ምዕራብ ጎጃም፤ ሁሉም የቤኒሻንጉል ጉምዝ ዞኖች፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ጉጂ፣ቶንጎ፤ ሸካ፣ ከፋ፣ ቤንች ማጅ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ ጌዲዮ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ ዞን 1 እና ጎደሬ እንዲሁም የሶማሌ ክልል ቆራሄ፣ ደጋህቡር፣ ዋርደር ዞኖች ይገኙባቸዋል፡፡


ምንም እንኳን በአንጻራዊ ሁኔታ በኖቬምበር 2022 ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የነበሩ የሚቲዎሮሎጂ ሁኔታዎች እየቀነሱ የሄዱ ቢሆንም፤ በኢሉባቦር፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጅማ የጋምቤላ እና ጎደሬና ዞን 2 ላይ ምቹ የአየር ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የጤና ሜቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ። በዲሴምበር 2022 እና በጃንዋሪ 2023 ወራት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የዝናብ ሁኔታው በመቀነሱና በተለየም በዲሴምበር ወር ይበልጥ ወደ ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ጥቂት ቦታዎቸ ላይ ብቻ ምቹ የአየር ጠባይ ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፤ ለመጥቀሰም ያህል ደቡባዊ የኢሉባቦር ዞን፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች  ይገኙበታል (ካርታ 3.3) ።




ካርታ 3.3: የበጋ 2022/23 በየወራቱ የነበረው ለወባ መራባት ምቹ ሁኔታ በቦታ ሽፋን

በሌላ መልኩ ከተስማሚ የአየር ሁኔታ (comfortable weather condition) አንጻር የተቀመረ የአማካይ የሙቀት መጠን (mean temperature) እና አማካይ የምዝን የአየር ርጥበት (Relative Humidity) መረጃ እንደሚያመለክተው ባሳለፍናቸው የበጋ ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ለመጥቀስም ያህል በአፋር፣ በጋምቤላ እና በደቡባዊ የሶማሌ ክልል በኦክቶበር በኖቬምበር እና በጃንዋሪ ተስማሚ ያልሆነ የአየር ሁኔታ እንደነበረ የተተነተነ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃ ያመለክታል።

በአጠቃላይ የ2022/23 የበጋ ወቅት ለወባ ትንኝ መራባትና መፈጠር የነበረውን ምቹ የአየር ሁኔታን ስንመለከት ከኦክቶበር ወደ ጃንዋሪ በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍል ላይ ከወር ወር እየቀነሰ መምጣቱን ማየት ተችሏል። በሌላ በኩል ያለፈው የበጋ ወቅት ለሰው ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታን (THI) ስንመለከት ከኦክቶበር ወደ ጃንዋሪ የምስራቅ እና ምዕራብ የሀገሪቱ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ የሙቀቱ ሁኔታ እየቀነሰ ሲመጣ በተመሳሳይ የአገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የቅዝቃዜው ሁኔታ ከወር ወደ ወር እየጨመረ መምጣቱን የተተነተኑ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 3.4) ::




ካርታ 3.4: የበጋ 2022/23 በየወሩ የነበረው ምቹ የአየር ሁኔታ በቦታ ሽፋን

# ምዕራፍ አራት

## የአየር ጠባይ፡ የበልግ ወቅት 2023 በግብርና፣በውሃውና በጤናው ዘርፍ ትንበያ

### 4.1 እ.ኤ.አ 2023 የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ በግብርና እንቅስቃሴ ላይ ሊያደርስ የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው እ.ኤ.አ 2023 የበልግ ወራት በአጠቃላይ ሲታይ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛውና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ግንዛቤ ተወስዷል። ይህም ሁኔታ ከላይ በተጠቀሱት የበልግ አብቃይ ለሆኑት አካባቢዎች የበልግ ሰብሎችን ለመዝራት

በጎ ጎን እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአካባቢዎቹ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላትም ሆነ በአፕሪልና ሜይ በሚገኘው እርጥበት በስፋት ለሚዘሩት በቆሎና ማሽላን ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ለመኸሩ የማሣ ዝግጅትም አሥተዋፅኦ ይኖረዋል። በመሆኑም የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ ለመጠቀም እና በወቅቱ የእርሻ ሥራን ለመጀመር ተገቢው ግብዓቶችን በማመቻቸት ከወዲሁ አስፈላጊው ዝግጅት መደረግ ይኖርበታል። በሌላ በኩል በሚቀጥሉት የበልግ ወራት በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች የሆነ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል ትንበያ ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በእነዚሁ በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በአካባቢዎቹ የተለመደውን የግብርና እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚችሉበት እድል ቢኖርም፤ ከመደበኛ በታች በተተነበየባቸው አካባቢዎች ሊከሰት የሚችለውን የእርጥበት እጥረት ለመቅረፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለዓብነትም ዝናብ ውሃ የማሰባሰብ የማቆርና በአግባቡ በመጠቀም ሊደርስ የሚችለውን ችግር ማቃለል ከመቻሉም በላይ አርሶ አደሮች በአጭር ጊዜ የሚደርሱና የእርጥበት እጥረትን ሊቋቋሙ የሚችሉ ሰብሎችን እንዲዘሩና ከተተነበየው የወቅቱ ዝናብ ዘግይቶ መግባት ጋር ትክክለኛና አስተማማኝ የዘር ጊዜ እንዲከተሉ እንመክራለን። በተመሳሳይም የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች የሚገኘውን ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ይገባቸዋል። እንዲሁም የሚጠበቀውን የእርጥበት እጥረት ችግር በተወሰነ ደረጃ ለማሻሻልና የሚገኘውን መጠነኛ እርጥበትም ቢሆን ጠብቆ ለማቆየትና በአግባቡ ለመጠቀም የአፈርና የውሃ እቀባ ስራዎችን ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ሁኔታውን በተወሰነ ደረጃ ማሻሻል ያስችላል። በተጨማሪም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛው በላይ ሊሞቅ እንደሚችል በተለይም በአንዳንድ ቆላማ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛው በላይ እንደሚሆን የሚጠበቀው የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከዝናብ እጥረትና መቆራረጥ ጋር በመዳመር ከእፅዋትና ከአካባቢያቸው የሚኖረውን ትነት ስለሚያባብሰው ዘመናዊ የውሃ አጠባበቅ ዘዴዎችን መከተል ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። በአንፃሩም የዝናብ እጥረት በሚጠበቅባቸው አካባቢዎች ከሚኖረው የእርጥበት መቆራረጥና የሙቀት መፈራረቅ ጋር ለፀረ ሰብል ተባይና በሽታ መከሰት አመቺ ሁኔታን የመፍጠር እድል ስላለው በተለይ የተባይ፣ በሽታ በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች ላይ በየጊዜው የማሳ ጉብኝት ማድረግና ሊከሰት የሚችለውን

ችግር ለማስቀረት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም በአንዳንድ አከባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ከማድረግ ጋር ተያይዞ በማሳ ላይ እሳት የመለኮስ ልማድ በመኖሩ ይህንንም ሁኔታ ተከትሎ የሰደድ እሳት እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥንቃቄ ከማድረግ ጎን ለጎን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ከወዲሁ እንዲከናወኑ ይመከራል።

በአጠቃላይ በወቅቱ  የሚጠበቀው የእርጥበት መጠንና ሥርጭት አብዛኛውን ጊዜ የሚስተዋለውን ከበልግ ወቅት ተለዋዋጭ የዝናብ ባህሪን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰጠውን ግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ በመውሰድና  ተግባራዊ በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊተጽዕኖውን መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ በስተመጨረሻም የተሰጠውን ትንበያና ቅድመ ማሰንጠንቀቂያ በጊዜና በወቅቱ ለውሳኔ ሰጪ አካላት በቶሎ ማድረስ አስፈላጊ እንደሆነና የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በየ 10 ቀኑ፣ በየወሩና በወቅቱ አጋማሽ የሚሰጠውን ትንበያና ምክረ አገልግሎት መከታተል እንደሚገባ እንመክራለን።

## 4.2 እ.ኤ.አ የ2023 በበልግ ወቅት የሚጠበቀው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የበልግ ወቅት ከፌብርዋሪ እስከ ሜይ ድረስ ያሉትን ወራቶች የሚያጠቃልል ሲሆን አብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች ከፌብርዋሪ የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው። ሆኖም የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች በመጠንም ሆነ በስርጭት ከፍተኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙት በማርች እና ኤፕሪል ወራት ነው።

ለበልግ 2023 የተሰጠው የአየር ጠባይ ትንበያ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ስንመለከት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች  እርጥበት እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፣የዝናቡ አጀማመር የተወሰነ መዘግየት ሊኖረው እንደሚችል ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በመጀመሪያዎቹ የበልግ ወራት በሁሉም የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ እንደሚያመዘንባቸው ይጠበቃል። ሆኖም ከማርች በኋላ የእርጥበት ይዘቱ በተለይም ከታችኛው የኦጋዴን ዋቤሸበሌ እና  ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶቸ በስተቀር እንደሚሻሻል ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት እንዲኖራቸው የሚያስችል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ግድቦች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ያስችላል።

በመሆኑም በውሃው ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አካላት የሚጠበቀውን መደበኛ እርጥበት በአግባቡ እንዲይዙ የሚመከር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ባሉ ተፋሰሶች የሚጠበቀው አነስተኛ እርጥበት በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ከወዲሁ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡

በአጠቃላይ የበልግ እርጥበት በተለያዩ ተፋሰሶች ላይ ቀስ በቀስ እየጨመረ እንደሚሄድ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ከሚኖራቸው በጎ ጎን በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጨ የሆኑ አካባቢዎች አስፈላጊው የቅድመ ጥንቃቄ ስራ እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡

## 4.3 እ.ኤ.አ በልግ 2023 ወቅት የአየር ጠባይ በማህበረሰብ ጤና ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የበልግ 2023 የሚጠበቀው የአየር ጠባይ በተለይም የመጨረሻዎቹ የበልግ ሁለት ወራት በሆኑት በሚያዚያ በግንቦት ሊኖር የሚችለው መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ፣ የምዝን እርጥብ አየር እና የሚጠበቀው ምቹ የሙቀት መጠን በተለይም በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አብዛኛው ቦታዎቻቸው ለወባ ትንኝ መፈጠርና መራባት ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በቀጣይ በልግ 2023 ለወባ መፈጠርና መራባት ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር የሚጠበቀው ከወቅቱ አጋማሽ በኋላ ቢሆንም በጥቂት አካባቢዎች ላይ ለመጥቀስም ያህል በአማራ፣በምዕራብ፣ በደቡብ ኦሮሚያ እና በሰሜናዊ የደ/ብ/ብ/ህ ክልል ምቹ እንደሚሆኑ የሚጠበቅ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት በተለይም ለወባ ተጋላጭ ለሆኑት ቦታዎች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲዲያደርጉ ይመከራሉ። በተለይም ለወባ መፈጠርና መራባት ምቹ የሆኑ የውሃ ማቆሪያዎችን ማፅዳት፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ታሰበው የተከማቸ ውኃን በማከምና ሌሎች በባለሙያዎች የሚሰጡ ምክሮችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

በሌላ በኩል የመጨው በበልግ 2023 የአየር ሁኔታ ተስማሚነትን ስንመለከት አብዛኛው የምስራቅ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ምስራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ የሙቀት ሁኔታው ከፍተኛ እንደሚሆንና የሚኖረው የአየር ሁኔታን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንዳለበት እየመከርን በየጊዜው የሚተነተኑ ወርሃዊና የወቅት አጋማሽ የጤና ሚቲዎሮሎጂ

መረጃዎችን ከኢንስቲትዩቱ ድረገጽ http://www.ethiomet.gov.et/bulletins/health_bulletins ላይ እንድትከታተሉ እንመክራለን፡፡

ለበለጠ መረጃ ከኢንስቲትዩቱ ድረገጽ https://www.ethiomet.gov.et ይመልከቱ